ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ
Unity University

ሐምሌ 21 ቀን 2010 ዓ.ም.

# 35ኛው የምረቃ ሥነ-ሥርዓት ላይ የተደረገ ንግግር

ክቡር፡ ዶ/ር አረጋ ይርዳው የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንትና የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር፣

የተከበራችሁ: የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ የሴኔት አባላትና ማህበረሰብ፣

የተከበራችሁ፡ ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፣ የእጩ ተመራቂ ቤተሰቦችና ውድ የዓመቱ እጩ ተመራቂዎች፣

ከሁሉ አስቀድሜ ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ለ35ኛ ጊዜ የሚያከብረውን የምረቃ በዓል ምክንያት በማድረግ ተሳታፊ ለመሆን በመሀከላችን በመገኘታችሁ እንኳን ደህና መጣችሁ እያልኩ የአክብሮት ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በምጣኔ ሐብትም ሆነ ለማህበረሰብ እድገታቸው ዛሬ ከፍተኛ ደረጃ ለደረሱ ሀገራት ትምህርት ትልቁን ድርሻ እንደሚወስድ ለሁላችንም ግልፅ ነው፡፡ በመሆኑም ሀገራት ይህንን የእድገት መሠረት የሆነውን ትምህርትን በተደራሽነትም ሆነ በጥራት እንዲስፋፋ ደፋ ቀና ሲሉ የሚስተዋሉት፡፡ በተለይ በማደግ ላይ ለሚገኙ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሀገራት ቁልፍ የእድገት መሣሪያ የሆነውን ትምህርትን ለሕዝቦቻቸው ማስታጠቅ በአለም ገበያም ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ግድ ይላል፡፡

የትምህርት ተደራሽነትንም ሆነ ጥራትን ከግብ ማድረስ የመንግሥት ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የግሉ ሴክተርም የራሱን ድርሻ መወጣት ይኖርበታል፡፡ ይህንን እውነታ በመገንዘብ የኢትዮጵያ መንግሥት የግል ባለሀብቶች በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ እንዲሳተፉ ባወጣው ፖሊሲ መሰረት፣ ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ በዚች ሀገር የግል የከፍተኛ ትምህርት ታሪክ ፈር ቀዳጅ (የመጀመሪያ) በመሆን ላለፉት ሁለት አሥርተ ዓመታት ከዲፕሎማ እስከ ድህረ-ምረቃ (የሁለተኛ ዲግሪ) ፕሮግራሞች ተማሪዎችን በመቀበል በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች በርካታ ባለሙያዎችን አስመርቋል፡፡